# የኢሳቱ ጋዜጠኛ ፋሲል የኔዓለም ; ጋዜጠኛ ወይስ መርማሪ ፖሊስ?

የኢሳት ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም፣ በፕሮፌስር ላጲሶና በአቶ ተክሌየሻዉ መካከል የተጠቀመባቸዉ የቃለ መጠይቅ ስልቶች ልዩነት  በትክክል አይቶ ለመለየትና የየራስን ፍርድ ለመስጠት ያስችል ዘንድ ለሁለቱም የቀረቡትን ጥያቄዎች በቅደም ተከተል መዘረዘሩ ተገቢ በመሆኑ እንደሚክተለዉ አቀርባቸዋለሁ።

ለፕሮፌሰር ላጲሶ የቀረቡላቸዉ ጥያቄዎች፡-

1. የኢትዮጵያ  ግዛት ከየት ነዉ የሚጀምረዉ?
2. የየትኛዉ ህዝብ ነዉ ኢትዮጵያዊ  የሚባለዉ?
3. የኩሽ እና የሴም እየተባለ መከፋፈሉ ትክክል አይደለም?
4. ቋንቋን መሰረት በማድረግ የተፈጠረዉ ክፍፍል እንዴት ነዉ?
5. ከአኩሱም ውድቀት በኋላ የአገዉ ሥርወ መንግስት ነበረ፤ ታዲያ የሰሜኑ ከደቡቡ እነዴት ተቀላቀለ?

6. ኦሮሞ ራሱን ችሎ ቆይቶ ነበር ማለት ይቻላል?

7. አማራ አለ የለም የሚሉ አሉ፤ እሰኪ የአማራን ታሪክ መነሻዉን ይንግሩኝ?

8. የአባ ባህሪን መጽሐፍ በተመለከተ እርስዎ የአለወት አስተያየት ምንድን ነዉ?

9. ለምንድን ነዉ ኦሮሞዎች የአባ ባህሪይን መጽሐፍ የማይቀበሉ?

10. ኦሮሞ ንጉሥ አዉራጅና ሿሚ ነበር ይባላል?

11. አጤ ምኒሊክ ኢትዮጵያን ሲያስፋፉ በኦሮሞ ላይ በደል ፈጽመዋል የሚባለውን እ ርሰዎ እንዴት ያዩታል?

12. የባህል መስተጋብር ነበረ፤ በትክክል  ይህ የኦሮሞ ይህ የአማራ  ባህል ተብሎ መለየት ይቻላል?

13. ልዩነት የሚፍጠረዉ በታሪክ መነሻ ነዉና የርሰዎ ሃሳብ በዚህ ላይ ምንድን ነዉ?

14. አሁን የአለዉ የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ አመት ነዉ ተብሎ ትምህርት እየተሰጠ ነዉ፤ እርሰዎ ምን ይላሉ?

15. ክብረ ነገስት ምንድን ነዉ?

16. ኦሮሞ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የፈጠረዉን የባህል ተጽእኖ እንዴት ይገመግሙታል?

17. ለኢትዮጵያ አንድነት ሲባል ታሪክ እንዴት ነዉ መጠናት ያለበት ይላሉ?

18. በታሪክ ላይ ያለው ልዩነት እያወዛገበን ነዉ፤ እንዴት ነዉ የሚፈታዉ?

19. አሁን ባነሱት ታሪክ ላይ አዳዲስ ታሪኮች ብቅ ብቅ እያሉ ነዉ፤ እርስዎ ምን ይላሉ?

20. ዛሬ አጤ ምኒሊክ በትግራይ ላይ በደል እንደ አደረሱ ነዉ የሚጻፈዉ፤ እርስዎ ምንይላሉ?

በሁለተኛው ክፍል ደግሞ አቶ ተክሌ የሻዉ፣ ፕሮፌሰር ላጲሶ በኢሳት ላደረጉት ታሪካዊ ቃለ ምልልስ አዉቀዉም ሆነ ሳያዉቁ ለሳቱት ስህተት የራሳቸው መጽሕፍት በእጄ ስላሉ እንዲያስተካክሉ ሃሳብ ልስጥ ብለዉ ኢሳትን ጠይቀዉ ከተፈቀደላቸዉ በኋላ ያቀረቡዋቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸዉ።

1. አቶ ተክሌ እርስዎ የታሪክ ባለሙያ ነዎት?

ሀ. የዚህ ጥያቄ አቀራረብ ጠያቂዉ እንደ አለመዉ አልተሳካለትም እንጂ የተናጋሪዉን ሞራል በመንካት ለሚቀጥሉት ጥያቄዎች የማዘናጊያና የማደናገሪያ ሀሳብ ለመፍጠር ታስቦ የቀረበ ነዉ::

ለ. ጋዜጠኛዉ በማንበብ ለሚገኘዉ እዉቀት ዋጋ የማይሰጥ መሆኑን ነዉ::

ሐ. የእዉቀት መለኪያዉ ስያሜ ብቻ እንደሆነ አመልካች ነዉ? የኛ ችግር ስያሜ አይደለም፤ ለተሰየሙበት ሆኖ መገኘት ነዉ:: ስያሜን ካነሳን እነመለስ ዜናዊ የኛን ዓላማ እስከ አስፈጻመ ድረስ ፊደል ያልቆጠረም ቢሆን ሚኒስቴር ይሆናል፤ ያለዉን በስያሜና በመመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ስምንተኛ ክፍል ያልድርሱትን ተምሮና ተመራምሮ እራሱን ለመጠበቅና ለማስከበር ሳይሆን ለነሱ ሰጥ ለበጥ ብሎ እራሱን አሳልፎ ለመሰጠት የሚያስችል ቅብ የትምህርት ሥርዓት ተዘርግቶ በአቋራጭ ያ ለምንም የእዉቀት መለኪያ ከሚማሩበት ሳይሆን

ከሚሰየሙበት የሲቪል ሰርቢስ ኮሌጅ ገብተዉ እየተሰየሙ በዶክትሬት የተጥለቀለቁ መኖራቸዉን ከዉያኔዉ ሰፈር ያሉትን ባለስልጣናት ማንነት ጋዜጠኛዉ ቢያዉቅ በስያሜ የሚያምንበትን ሃሳብ እንዲመረምር ሳይረዳዉ አይቀርም ።

2. በእርስዎ እይታና ባለዎት ግንዛቤ ታሪክን መጻፍ ያለበት ማን ነዉ?

3. የጥንቱን የኢትዮጵያ ታሪክ የጻፈዉ ማነዉ? በማከታትል የጽሑፍ ባህልና ልምድ ያላቸዉ እነማን ናቸዉ ?

4. ሁሉም ምሁራን የሚሰማሙበት ኢትዮጵያዊ ታሪክ አለ ወይ?

5. አሁን ያለዉ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለው ታሪክ ተጽፏል ወይ?

6. ፕሮፌሰር ላጲሶ የኢትዮጵያ ታሪክ ተረት ተረት ነዉ፤ አላሉም።በማለት ማብራሪያ ሰጥቶ አቋረጠ።

7. ፕሮፌሰር ላጲሶ የሳቱአቸዉን 1፣ 2፣ 3፣ብለዉ ይዘርዝሩልኝ?

8. ፕሮፌሰሩ ያሉት የኢትዮጵን ታሪከ የጻፉት ደብተራዎች ናቸዉ፤ እንጂ ሌላ አላሉም። የህዝብ አይደለም ነዉ ያሉት

ብሎ ይጠይቃል?

9. አሁን በዩንቨርሲቲ እየተጠና ነዉ፤ የዚህ ችግር ምንድን ነዉ?

10. ፕሮፌሰሩ ያሉት እኔ እንደማስበዉ ደብተራዎችም አጠቃለዉ ስላልጻፉ ነዉ በማለት የፕሮፌሰሩን ሃሳብ አብራራ?

11. ፕሮፌሰሩ ከተናገሩት አንዱ አማራና ኦሮሞ ነዉ፤ እያሉ የአማራን ታሪክ እንዴት አዋረዱት ማለት ይቻላል?

12. አማራ የሚባለዉ በታሪክ የየትኛዉ ክፍል ነዉ?

13. የኢትዮጵያ ታሪከ የሁሉም ከሆነ በተለያየ አቅጣጫ ሲተች ለምንድን ነዉ? የአማራ ታሪክ ተተቸ የሚባለዉ?

14. ለአድማጩ ግልጽ እንዲሆን የኢትዮጵያ ታሪክ የአማራዉ ብቻ ካልሆነ ታሪክ ሲወቀስ አማራዉ ተነካ ይባላል፤ለምን?

15. እነከሌ አማራ ናቸዉ አይደሉም ለማለት መስፈርቱ ምንድን ነዉ?

16. የዚህ ነገድ ነዉ የምንለዉ በምን መስፈርት ነዉ? አማራ አይደሉም፤ ሲባል መስፈርቱ ምንድን ነዉ? በአካባቢዉ

በመወለዱ ነዉ ?

17. ነገሩን ፈር ለማሳዝ ቢቻል ጥሩ መሰለኝ። ነገስታት

በዘር የጠሩ አማራዎች አይደሉም ነዉ፤ የሚሉት?

18. የእርስዎ ተቃዉሞ የሰለሞን ስርወ- መንግሥት ሰዎች

የኢትዮጵያ እንጂ የአማራ አይደሉም ነዉ፤ የሚሉት?

19. ፕሮፌሰሩ ትክክል አይደሉም፤ ብለዉ የሚከራከሩባቸዉ

ምን ምን ናቸዉ?

20. በሶስተኛ የሚያነሱት ተቃዉሞ ምንድን ነዉ?

21. ደቡብ ጫፍ ድረስ የአክሱም ግዛት ነበር?

22. የጥንቱ አማራና የአሁኑ አማራ አንድ ነዉ፤ ወይ? ብሎ

ጠየቀ::

ይህ የጋዜጠኛዉ ጥያቄ የጥንቱና የአሁኑ ብሎ አማራን ከፋፍሎ ማቅረቡ ለምን ዓላማ ታሰቦ እንደሆነ አደማጩ በተለይ አማራዉ ልብ ሊለዉ ይገባል ::

23. አማራዉን ለማጥቃት ሲሉ የትኛዉን አማራ ነዉ?

24. ፕሮፌሰሩ የአማራ ምሁር አጨማለቀው ከሚሉት የኢትዮጵያዉ  ቢሉ ይስማማሉ?

25. እኔ የተረዳሁት አማራም የነበረ ነዉ፤ ኦሮሞም የነበረ ነዉ፤ ያሉት ብሎ ሀተታዊ ጥያቄ አቀረበ ።

26. ክብረ ነገስት የሥልጣን አያያዝን ቢያካትትም ስለሰለሞን ዘር ነዉ የሚናገረዉ፤ ይህንን እርስዎ ይቀበሉታል?

27. የፖለቲካንና የታሪክን አንድነት ቢያስረዱኝ?

28. አሁን የታሪክ ጉዳይ እያወዛገበ ስለሆነ እንዴት ነዉ የሚፈታዉ?

ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም ከመዉያያዉ ርእስ ዉጭ እራሱ ጠይቆ እራሱ የመለሰዉ እረስዎ በደርግጊዜ የሰርቶ አደር ጋዜጣ አዘጋጅ ነበሩ ይባላል። እኔ ግን አላዉቅም፤ በማለት ሁለቱንም የማይመለከታቸዉን ጥያቄ እዚህ ላይ ማንሳቱ አቶ ተክሌ በደርግ ዘመን መስራታቸዉን እንደወንጀል አድርጎ በማቀረብ የማሸማቀቅ ስራ የሰራሁ መስሎት እንደሆነ አድማጭ ይረዳዋል። አቶ ተክሌ ከደርግ ጋር መስራት ብቻ ሳይሆን የዉያኔ መሪዎች ወላጆችንና ዘመዶችን የርዕዮት አለም ትምህርት ያስተምሩ እንደነበር የአሁኑ ባለስልጣኖች የዚያን ጊዜ ወንበዴዎች ከማንም በበለጠ አበጥረዉ ያዉቁታል።

በመሆኑም  ለአድማጩ ግራ የገባዉ ጋዜጠኛዉ ያቀረበዉ ሪፖርት ለማን እንደሆነ ነዉ::

 በአጠቃላይ ከአቶ ተክሌ ጋር በተደረገዉ ቃለ ምልልስ እሳቸው ለሚቀርብላቸዉ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሲጀምሩ በእያንዳንዱ ጥያቄ የተሟላ መልስ እንዳይሰጡ የተደረገዉ ግርገራና የሀሳብ ማዘናጊያ ማብራሪያዎች ምንያህል የጠነከሩ እንደሆኑና ከፕሮፌሰር ላጲሶ የጊዜ ፍጆታ ጋር ምን ያህል ልዩነት እንዳላቸዉ አድማጩ ይፍረደው።  ለማስረጃ ይሆን ዘንድ ለፕሮፌሰሩ ከቀረቡት  ሀያ ጥያቄዎች  ከ3ኛዉ፣ ከ14ኛዉ እና ከ20ኛዉ  በስተቀር አስራሰባቱም ጥያቄዎች ያለምንም ግርገራና መሰናክል ሙሉ ጊዜአቸዉን ተጠቀመዉ እንዲመልሱ እድሉን ሰጥቷቸዋል።  ነገር ግን አቶ ተክሌ የሻዉ ከተሰጣቸዉ ሀያ ስምንት ጥያቄዎች በሰባቱ ጥያቄዎች ላይ ሙሉ ጊዜያቸዉን ተጠቅመዉ እነዲመልሱ እድል ሲሰጣቸዉ ሃያ አንዱን ጥያቄዎች ሙሉ ጊዜያቸዉን ተጠቅመዉ መልሳቸዉን አሟልተዉ እንዳይመልሱ መሰናክል፣ ግርገራና ንትርክ በጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም ተፈጽሞባቸዋል።  አንባቢያን ይህን ጽሑፍ ከተሰጠዉ ቃለምልልስ ጋር በማገናዘብ የየራሳቸውን ፍርድ እንዲሰጡ  ጸሀፊዉ ይጠይቃል::

አቶ ፋሲል፣ እንደጋዜጠኛ ያለምንም አድልዎ ጠይቆ ለአድማጩ ማሰማት ሲገባዉ ለጊዜዉ ከጥቂት አማራዎች በስተቀር አብዛኛዉ ሊረዳዉ በማይችል በሻሸ የተጋረደ አድልዎ ፈጽሟል፡፡ በመሆኑም ሴራዉን ከተረዱት የአማራ ህዝብ ተቆርቋሪዎች ከራሱ ባለቤት ጀምሮ በተሰጠዉ መራራ አስተያየት ምክንያት ከዚህ የዳንኩ መስሎት በጻፈዉ ደብዳቤ እራሱን ከሳት ወደ እረመጥ ከትቷል፡፡ ከዚህ በላይ እሱና የኢሳትጋዜጠኛ ባለደረቦቹ በአማካሪዎቻቸዉና በአለቆቻቸዉ አማካይነት በወያኔዎቸ ሴራ እየጠፋ ያለዉን የአማራ ህዝብ ጩኸትና ዋይታ ሌላዉ ወገኑ እነዳይሰማ፤ ተደብቆ በርብርብ ለማጥፋት የተወሰነዉን ዉሳኔ ለማሳካት ስለአማራ ህዝብ የሚቆረቆሩ በኢሳት መድረክ ትርዉ እነዳይሉ የወሰኑ ለመሆናቸዉ ይህ አረጋጋጭ ነው፡፡ በአጋጣሚ የአማራዉ ተቆርቋሪ የሆኑ መልስ ለመስጥት ቢቀረቡም በማዋከብ፣ በማደናገር፣ በመገርገር፣ ብሎም በማሸማቀቅ ያሰቡትን ሀሳብ በትክክል እንዳያስተላልፉና ተደብቆ እንዲቀር ጋዜጠኛ ፋሲል በአቶተክሌ የሻዉ ቃለምልልስ ላይ ያሳየዉን የመሰሪነት ስራ መስራት እንዳለባቸዉ በምክክር የኢሳት ኤዲቶሪያል ቦርድ መወሰኑን የፋሲል የኔየአለም ደብዳቤ ያስረዳል ::

 አቶ ተክሌ የሻዉ የሚያሰተላልፉትን በጽሁፍ ሲገልጹልኝ አንብቤ የተሰማኝን ጻፍኩላቸዉ። አንደኛዉን ሀሳብ ተቀበሉኝ። ሁለተኛዉን ግን እሱን ለኔ ተወዉ አሉኝ። በእኔ በኩል ከጻፏቸዉ መካከል አንደኛዉ በቀጥታ ቢተላለፍ ኢትዮጵያ ዉሰጥ ከፍተኛ አደጋ የሚያመጣና በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ አማሮችን ብቻ ሳይሆን መላዉን ህዝብ ለእልቂት የሚዳረግ ከፍተኛ የታሪክ ጠባሳ ጥሎ የሚያልፍ ነገር መሆኑን አመንኩ። ይህን ማስተላለፍ እንደማይቻል ጻፍኩላቸዉ። ይህን አደገኛ መልእክት በመላዉ አገሪቱ እየታየ ባለዉ ኢሳት ቢተላለፍ ኑሮ ኢሳትም ሆነ እኔ ራሴ ዘላለም የምጸጸትበት በወንጀልም የምጠየቅበት በተለይም ሌት ከቀን ለአገራቸዉ የሚለፉትን ባለደረቦቸን መግደል ይሆንብኝ ነበር:: በዚህ ምክንያት አቶ ተክሌ እንዳሰቡት እንዳይናገርብኝ ምን ማድረግ አለበኝ በማለት ከራሴም ከባልደረቦቼም ጋር መክሬመሰረዙ ወይም ቆርጦ ማሰቀረቱ ለሀሳብ ነጻነት የሚታገሉ ሰዎች የሰዎችን ሀሳብ የሚያፍኑ ከሆነ ትግላቸዉ የዉሸት ነዉ ስለሚባል፤ በሚል ፍርሀት የመረጥኩት የግርገራ፣ የማዘናጋት፣ ሃሳብን የማደናቀፍ ስራ፣ ጣለቃ በመግባት ሙሉ ሀሳባቸዉን ለህዝብ እንዳያስተላልፉ ማድረግን፣ መርጬ ጣልቃ እገባ ነበር

ይህንም አዉቄ አስቤበት አልሜ የፍጸምኩት ነዉ፤ ሲል ከሊቅ አስከ ደቂቅ በአማራ ላይ የተሰራበትንና እየሰሩበት ያለዉን መሰሪነት ጎልጉሎልናል ::

ከተዘከዘከልን የኢሳትንና የአለቆቹን ዓላማ የያዙትን ጽንሰ ሃሳቦች ጥቂቶችን እንይ።

በማለቅ ላይ ላለዉ የአማራ ህዝብ ተቆረቋሪ የሆነዉ የሞረሽ ወገኔ የአማራ ሲቪክ ድርጅት አማራዉ እንደማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ብሄረሰብ የተጎዳ፣ የተበደለ መሆኑን ቢያዉቅም ወያኔ ሲሸፍት ጀምሮ ከሌላዉ በተለየ አማራዉን ለማጥፋት አልሞ በአለመዉ መሰረት፡-

ሀ. በኢትዮጵያ ዉስጥ አትኖርም ተብሎ በአጋሮቻቸዉ ንብረቱ እየተቀማ፣ እየተገደለ ባለማቋረጥ ሲባረር እያየን

ለ. ህዝቡ እነዳይራባ ማምከኛ እየተሰጠዉ የዚህ ዉጤት አምስት ሚሊዮን አማራ መቀነሱን እየነገሩን የወገን ያለህ አለቅን ብሎ እሪታዉን ጩኸቱን ከወያኔና ከአጋሮቹ ዉጭ ላለዉ ኢትዮጵያዊ ወገኑ በሲቪል ድርጅቱ በኩል በቀጥታ ቢተላለፍ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከፍተኛ አደጋ

ያመጣል አለ:: ይህ አረፍተ ነገር የሚነግረን ጋዜጠኛ ፋሲል የኔ አለም እንድታልቅ የተፈረደብህ አማራ አንተ ከየአለህበት እለቅ እንጂ ባንተ እዳ ማን ሊያልቅልህ ነዉ የምትፈልገዉ ሞኝህን አሞኝ የአንተን መከራና እልቂት ብናገር የአማራዉ ህዝብ ከሰማ ከጡላቱ ጋር ይተናነቃል፤ በዚ ህ የተነሳ ሌላዉም ያልቃል፤ የውያኔ ግዛትም ይናጋል፤ ስለዚህ ጭጭ ብለህ እለቃት የሚል መልእክት ነዉ::

በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ አማሮችን ብቻ ሳይሆን መላዉን ህዝብ ለእልቂት የሚዳርግ ከፍተኛ የታሪክ ጠባሳ ጥሎ የሚያልፍ መሆኑን አመንኩ አለ፤ ጋዜጠኛ ፋሲል በጽሁፉ። ይህ አረፍተነገር የሚነግረን እሰካሁን አማራዉ በተለያዩ ክልሎች እያለቀ እንደሆነ እናዉቃለን። አማራዉ አይሰማም፤ ልብ የለዉም እንጂ እልቂቱን ትንፍሽ ላንል በቃል ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ በደብዳቤ ገልጫለሁ። አሁንም ልድገመዉ የአማራን ማለቅ በኢሳት ብናስተላልፍ መላዉን ህዘብ ለእልቂተ የሚዳርግ በመሆኑ እና የታሪክ ጠባሳዉም በሁሉም ላይ ጥሎ ከሚያልፍ አንተ በወያኔዎች አህያ ተብለህ የተሰየምክበትን ጭነት የምትችለዉ አማራ አሁንም ከዚያዉ ቻለዉ። የታሪክ ጠባሳዉም በአንተዉ ላይ

ከአንተ ጋር ይሙት ነዉ እኮ የምንልህ፤አይገባዉም እንዴ ይህ አማራ ማለት? የሚል መልእክት ነዉ ::

ይህ አደገኛ የአማራዉ እልቂት መልእክት በመላዉ አገሪቱ እየታየና እየተሰማ ባለዉ ኢሳት ጀግና ሆንኩ እንጂ ቢተላለፍ ኑሮ ኢሳትም ሆነ እኔ ዘላለም የመጸጸትበት በወንጀልም የምንጠየቅበት ይሆን ነበር፤ አለ ጋዜጠኛ ፋሲል።

ይህ አረፍተ ነገር የሚነግረን ኢሳትለሚያሰተላልፈዉ ዜና የበላይ ጠባቂ እነዳለዉና የአማራን እልቂት ማሰማቱ ለአማራዉ ህዝብ መፍትሄ የሚያሰገኝ አማራን ለማጥፋት ከተሰለፉት ከበላይ ጠባቂዎቻቸዉ ጋር የሚያጋጨቸዉ በመሆኑ ስለአማራዉ ምንም እንደማይተነፍሱ የሚያሰረዳ መልእክት ነዉ::

በተለይ ሌት ከቀን ለአገራቸዉ የሚለፉትን ባለደረቦቸን መግደል ይሆንብኝ ነበር፤ በማለት ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም የሚቆጨው፤ እኔስ የሆንኩትን ልሁን ፤ያላሉኝን የአማራዉን ተቆርቋሪ ሲያቀብጠኝ ጠይቄ፤ የማደናገሪያ ስልት ፈጠርኩ ብየ፤ አፌን እያዳጠዉ ሊደበቅ ያለቻለ ጥፋት ሰርቻለሁ። የማዝነዉ ሌት ከቀን ለኢትዮጵያ ለሚለፉት፣ ከአማራዉ ዉጭ ለሆኑት፣ ኢትዮጵያዊያን ባለደረቦቸ፣

በዚህ ሙት ይዞ ይሞታል በሆነ የአማራ ስበብ አማካኝነት ጉዳት ማምጣቴ ነዉ እንጂ ብሎ፤ ስለ አማራዉ ህዝብ ማለቅ ሳይሆን ስለጓደኞቹ መጸጸቱን የሚገልጽ መልእክት ነዉ ::

ስለዚህ ጠላትና ወዳጅ መለየት የሚያስችል አዕምሮ ያለህ አማራ የፋሲል የኔአለም ደብዳቤ የሚነግርህ ‹ኢሳት የሰፈዉ ህዝብ ዐይንና ጆሮ›፤ የምንለዉ አማራን ሳይጨምር ሌላዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ነዉ::የሚል ነዉ።

አማራን ከገባበት ትብተባ ይወጣ ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳዉ!!

ከታዛቢዎች አንዱ

ዋሽንግተን ዲሲ፣ አሜሪካ።